መስከረም ፮ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.

# አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ!

ርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ ክርስቲያን

ዋሺንግተን ዲሲ

ሊቀ ማእምራን አማረ ካሣዬ የሰጡት መግለጫ

“አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! እግዚአብሄር ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ ! ዛሬ የምታዩቸውን ግብጻውያን ዳግም አታዩዋቸውም ! ” (ዘጸ 14፡13)

1ኛ፡ በቋሚነት ተመዝግባችሁ መተዳደሪያ ደንቡን አዘጋጅታችሁ፤ ያዘጋጃችሁት መመሪያ የሚጠይቃችሁን አሟልታችሁ በቅርብ ሆነው እየጠበቁ እንዲያስተዳድሩ ባለደራ ቦርድ መርጣችሁ የሰየማችሁ የርእሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አባላት ፤

2ኛ፡ የተሰየማችሁለት ጊዜ ደርሶ አደራውን የሰጣችሁ ጠቅላላው ጉባኤ (ባለ ንብረቱ) ማህበረ ምእመናን ሀላፊነቱን እስኪረከባችሁ ድረስ አደራውን ለመጠበቅ በመታገል ያላችሁ ባለ አደራ ቦርድ አባላት፤

3ኛ፡ በቋሚ አባልነት ተመዝግባችሁ ወርሀዊ አስራት ባትከፍሉም በጸሎትና በሀሳብ ከኛ ጋራ ያላችሁ ወገኖቼ በሙሉ፤ ይህች የምስክርነት ድምጼ ትድረሳችሁ እያልኩ “አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! እግዚአብሄር ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ ! በሚለው በነቢዩ ቃል ያቀረብኩላችሁን የምስክር ድምጼን በትእግስት እንድትሰሙ እማጸናችኋለሁ።

ሙሴ ይህን ቃል የተናገረው ህዝቡና እሱ ከነበሩበት ችግር ወደ ተሻለ ተሰፋ ምድር ለመድረስ በጉዞ ላይ ሳሉ ያልጠበቁት ተስፋ አስቆራጭ ፈታኝ አጣብቂኝ ሁኔታ ላይ በደረሱበት ወቅት ነው። ወደ ተስፋ ምድር በመገስገስ ላይ ሳሉ ከኋላቸው ሊደመስሳቸው የተዘጋጀው ሰራዊት እየተከተላቸው በራሳቸው ሃይል ሊሻገሩት ከማይችሉት ባህር ላይ ደረሱ። በዚህች ቅጽበት ሙሴ “አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! እግዚአብሄር ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ ! አላቸው። መታደግ ብቻ አይደለም። “ዛሬ የምታዩቸውን ግብጻውያን ዳግም አታዩዋቸውም” አላቸው። ቀጠለና “እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል። እናንተ ያለባችሁ መታገስ ብቻ ነው” (14) እያለ ከሽብር ወጥተው ከተረጋጉ እና በእምነታቸው ባንድነታቸው ጸንተው ከቆሙ የሚዋጋላቸው እግዚአብሄር እንደሆነ ነገረቻው። ጸንተው ተባብረው በመቆማቸውም፤ ሙሴ እንዳለው እግዚአብሔር ባህሩን ከፍሎ በማሻገር ታደጋቸው። ባህሩንም አስቆጥት የፈሮንን ሠራዊት በመደምሰስ ተዋጋላቸው። ከዚያ በኋላ ያሰደዷቸውን ግብጻውያንን ዳግም አላዩም። በዚያች ፈታኝ ወቅት ሙሴ ከፈሮን ሠራዊት ጋራ ወደ መስጠም ወይም ወደነበሩበት የጨለማ ጉዞ ለመመለስ ከመግፋት ይልቅ ከሚገፉትና በግፍ ከሚሳደዱት ጋራ አብሮ እየተሰደደና እየተበደለ “አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! በሚል ቃል እያረጋጋ ሀለፊነቱን ለመወጣት እንደመከረ እኔም አቅሜ የፈቀደለኝን ሃላፊነት ለመወጣት እሞክራለሁ።

## የኔ ሃላፊነትና ላደርገው የምችለው

በዚህ ወቅት እኔ ላደርገው የምችለው እግዚአብሔር የሚዋጋላትን መስዋዕት የምታስከፍለውን እውነትን መናገር ብቻ ነው። አብሮ መኖር የሚያስከትላቸው አብሮ መብላትና መጠጣት ብቻ አይደሉም። ሲሳሣት በመጋረድንና ሲዋሽ በመሸፈን ከራስ ሕሊና ጋራ መጋጨትንም ያስከትላል።

ሌሊት ከቤቴ ወጥቼ ማታ ወደ ቤቴ የምገባው፤ መተዳደሪያ መመሪያ አዘጋጅታችሁ መመሪያችን የሚፈቅደውን አሥራት እየከፍላችሁ የምትንከባከቧትን ቤተ ክርስቲያን እናንተን ወክለው እንዲጠብቁላችሁ የመረጣችኋቸው የቦርድ አባላት መታዘብና መመልከት ብቻ ሳይሆን የናንተን የጠቅላላ ምእመናኑን ሁኔታ እመለከታለሁ። ከባለ አደራ ቦርድ እና ባለንብረቶች ከጠቅላላው ጉባዔ ይልቅ በየደቂቃው ወደዚህች ቤተ ክርስቲያን እየጎረፈ የሚገለገለውን ህዝብ ከኔ በተሻለ በቅርብ ተመልክቶ የተረዳ ያለ አይመስለኝም።

በመካከል በመገኘት ቢቻል መገላገል፤ ባይቻል ግን በአባልነት የተመዘገቡ ሰዎች በማስረጃ የሚያወግዙትን ለቤተ ክርስቲያን ክብርና ቅድስና ሲባል በአባልነት ባይመዘገቡም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና አካል ከሆነ አባላቱ ያሰለፉትን ውግዘት መደገፍ ተገቢ ነው። ይሁን እንጅ

አብሮ  መብላትና አብሮ ማደግ በሚፈጥረው ተጽእኖ  ግፊት አሁን ይህን በመሰለ  ሁኔታ  የተቀሰቀሰቀሰውን  ጫጫት ለመደገፍ የሚሰለፉትን ድምጽ መስማት ተቀባይነት የለውም። በደንባችን መሰረት የተመዘገቡ አባላት እንኳ ቢሆኑ በዚህ መልክ በህገ ወጥነት በሚፈጥሩት ውካታ ግራ ተጋብቶ  ከመስመር የወጣውን ስብሰባ ማስተናገድ  ለቤተ ክርስቲያን  አባላት ቀርቶ ለእድር አባላት የሚዋጥ አይደለም ።

አብሮ በመብላትና በመኖር በጓደኝነት ከሆነ፤  አሁን  ቆሞስ ነኝ ከሚሉት  ከታደሰ ሲሳይ የሚቀርበኝ ሰው አልነበረም። በቤተ መቅደስ አገልግሎት አብረውኝ ባይሰለፉም፤ አቶ አዲሱና ዶክተር አክሊሉ  የምቀርባቸው ወገኖቼ ናቸው።  ነገር ግን እየተመላለሱ ወደ ቦርድ በመግባት ለብዙ አመታት አብረውኝ ከቆዩት ሰዎች ያላየሁትን እውነት ሞራልና የመንፈስ ጽናት አሁን ከተመረጡት ቦርዶች በማየቴ እጅግ ረክቻለሁ።  ይህን በግልጽ ባልመሰክር መቁረብ የማልችል "ጳኡ ንዑሰ ክርስቲያን" ብሎ ከቤተ ክርስቲያችን እንዲወጡ  ቀኖናችን ከሚያዝዛቸው ካልተጠመቁ ክርስቲያኖች  በታች እራሴን እጅግ ማሳነስ ነውና  አላደርገውም። ስህተቱን ህሊናየ እያወቀው መደገፍ ክህደት እንጅ ትህትና ማሳየት አይደለም። ተሳሳታችኋልና ተመለሱ ማለትም ማዋረድ አይደለም።

በአድማ የተነሳሱትን  እነዚህን ሰዎች ገና አድማቸውን ሲጀምሩ የተቃወምኳቸው፤ አሁን የተከሰተውን አደጋ በመረዳት ነበር። ይህን በመሰለ ህገ ወጥ አድማ እየተገፉ ስህተት ከሚፈጽም ቡድን ጋራ ተባብሬ  ከመከበር ይልቅ፤  እንደኔ በቅርብ ሆኖ የሚሰሩትን ተንኮልና አድማ ላልተመለከተው ለጠቅላላ ጉባዔውና ለተሳላሚውም ህዝብ የታየኝን ችግር በመግለጹ መዘለፍና መዋረድ እንደ ክብር እቆጥረዋለሁ።

የፈለጉትንና አቅማቸው የፈቀደላቸውን ተጽእኖ  ለማክበድ ቢረባረቡብኝም፤ አስቀድሜ በመናገሬ እጅግ ደስ ይለኛል። አሁን "ከናንተ ጋራ በነበርኩ ጊዜ በሙሴ ሕግ  በነብያትና  በመዝሙር መጻሕፍት  ስለኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ  ይገባል ብየ  የነገርኳችሁ ቃሌ ይህ ነው" (ሉቃስ 24፡ 44) ብሎ  ጌታችን የተናገረውን ሳስበው ትልቅ እርካታ ይሰማኛል። ለጠቅላላው ህዝበ ክርስቲያን ያየሁትንና የተረዳሁት በዚህች ሰአት በግልጽ ባልመሰክር ኖሮ፤ ሀላፊነቴን ባለመወጣቴ እየዋለ እያደረ የሚነድብኝን ህሊናዊ ወቀሳ የማብረድ እድሉን ሳላገኝ ወደ መቃብር እሄድ ነበር ብየ እገምታለሁ።

## <u>ለጠቅላላ ህዝበ ክርስቲያን</u>

የቤተ ክርስቲያናችንን ስርአት በመከተል የምንኖርበት አገር ህግ በሚፈቅደው መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅታችሁ አስራታችሁን እየከፈላችሁ ለራሳችሁና ተበታትኖ ላለው ሮጦ ለሚያድረው ህዝብ ወደ ፈጣሪው መማጸኛ እንድትሆን በምትመሯት ቤተ ክርስቲያን አስተዳደሩንና ገንዘቡን እንዲቆጣጠሩ ባለ አደራው ቦርድ መርጣችሁ የሰየማችሁ ወገኖቼ!

የሰየማችሁት ባለ አደራ ቦርድ ከናንተ ከጠቅላላ ጉባዔው ጋራ እየተወያየና እያስፈቀደ  በባለ ሙያወችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋራ በመነጋገር   ካሰባችሁት ተስፋ ለመድረስ ጉዞ ጀምረን ነበር።  አሁን በስግብግብነት በተንኮልና በሸር የተነሳሱ ጥቂት ወገኖቻችን ከታቀደው ስራ ይልቅ እኛ እንብላው በሚል የተነሳሱና፤ አምላክን ከመስማት ይልቅ የኛን ቃል ስሙ፤ በሚል በግል ክብርና ዝና የሰከሩ   ጥቂት ሰዎች እራሳቸው ጠፍተው ይዘውን ለመጥፋት ያየነውን የተስፋ  ብርሃን አጨለሙብን፤ በጀመርነው  የተስፋ ጉዞ ላይ አሚከላና እሾህ  ነሰነሱብን፤ አሽከላና ወጥመድ ዘረጉብን።

እናንተ (ጠቅላላው አባል) በተስማማችሁበት ነገር ሁሉ በግላዊ ፍላጎትና ሸር የሰከሩ ጥቂት ሰዎች አብረው የተስማሙበትን አፍርሰው  የተዘረጋውን እቅድ  ከደው በቤተ ክርስቲያን  ላይ ዘመቻቸውን ከፈቱ።  ጠቅላላው ጉባዔ  መርጦ በሰየመው ቦርድ ላይ ጠለፋ ዘረጉ።  በሙሴ ዘመን የተከሰተው ወንድም ወንድሙን እንደጠለፈው እና እንደገደለው ያለ ነገር  በመካከላችን ፈጠሩ።  መንገዳችንን ሁሉ የበርሀ አሸዋ መድረሻችንንም ባህረ ኤርትራ አደረጉት። በእምነት በህግና ስርአት የምንመራ እንዳልሆን አድርገው  ከህጋችንና ከስርአታችን  ጋራ በሚጋጭ ጫጫታና ረብሻ ሊያፈርሱን ሞከሩ።

"እግዚአብሔር ባሳየዎ ክርስቶስ ባመለከተዎ" ይፍረዱ እያሉ ሚዛናዊ ዳኝነት ለማግኘት ይጥሩ በነበሩት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን መንፈስ በመከተል የቀናውን መውጫ መንገዳችን መከተል ይኖርብናል። ይህም ሙሴና ህዝቡ በተመሳሳይ ፈተና ላይ በወደቁ ጊዜ "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል። እናንተ ያለባችሁ መታገስ ብቻ ነው" እንዳለው፤  ውጊያውንና ድሉን ለእውነት ባለቤት ትተን፤ በትእግስት በእምነት ቅዱሳት መጻህፍትን ቀኖናውንና ቃለ ዓዋዲውን መተዳደሪያ ደንባችንን መከተል ነው።  መታገስና በእውነት ጸንቶ መቆም ነው። የሚዋጋውም እግዚአብሔር እንደሆነ ማመን ነው።

# <u>ለባለ አደራ ቦርዱ</u>

አደራውን በሰጣችሁት በናንተ በጠቅላላው ጉባዔ ፊት፤ የቀኖና መጻህፋችን፤ ቃለ ዓዋዲውና መተዳደሪያ ደንባችን የሚያስጠነቅቁትን ብታውቁም፤ ለአጽንኦ በመጥቀስ ለባለ አደራው ቦርድ ማሳሰብ እወዳለሁ። "ዘተወክፈ ማኀጸንተ ይደልዎ ከመ ይዕቀባ በዓቢይ ጻሕቅ ወይኩን ዐቂቦቱ ኪያሃ ከመ ንዋዩ ። ወለእመ ጠፍአት እምድህረ መጠዋ አልቦቱ ዕዳ". . . . . "ወይደለዎ ለአማኅጸኒ ወለዘአማኀጸኡ ሃቤሁ ማኀጸንተ ጊዜ ፈቀደ ኀበ ዘይትከሀሎ ለዘአማኀጸኡ ኀቤሁ ከመ ይመይጥ ኪያሃ ለአማህጸንያን ከመ ይትመጥውዋ። ወለእመ አበየ ዘንተ ትከውን እዳ ላዕሌሁ " (አንቀጽ 29፡ 1 ሺ 22) ። ማለትም፡- አደራ የተቀበለ ታማኝ; ለግሉ ንብረት በሚያደርገው አጠባበቅ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት የሚከፍለውን፤ ለተቀበለው አደራ መክፈል አለበት። የሚያስረክብበት ጊዜው ደርሶ ለባለቤቱ ላለማስረከብ ምክንያት እየፈለገ ፈቃደኛ ካልሆነ ግን በባለ ንብረቱ ተጠያቂ ባለእዳ ይሆናል። የኔም ሀላፊነት እዚህ ላይ ይፈተናል።

አደራ ሰጭው ብዙሀኑ ሳይስማማ በራሳቸው ፍላጎት የተወሰኑ ግለ ሰቦች ተነሳስተው በህግና በባለ ንብረቱ ድምጽ የተመረጠውን ባለ አደራ ቦርድ ያለ ህግና ስርአት ጫጫት ፈጥሮ ይውረድ ማለት ህጋችን የማይፈቅደው ስለሆነ የምቀበለውና የምስማማበት አይደለም። በዚህም አቋሚ የስም ማጥፋት ዘመቻ ይቅርና የሚጠይቀውን መስዋእት እከፍላለሁ ያልኩትም ስለዚህ ነው። ስለዚህ ባለ አደራ ቦ ርዶች አደራውን የሰጣችሁ ህዝብ እስኪረከባችሁ ጸ ንታችሁ ቁሙ! ወደ <u>ቃለ ዓዋዲ</u>ው እሻገራለሁ።

# <u>ቃለ ዓዋዲ</u>

መንግሥት በሰየመው ፓትርያርክ በእጅ አዙር ሊቆጣጠረን በመሞከሩ፤ ከመንግስት ቁጥጥር ለመራቅ ከሚሰይማቸው ፓትርያርክ አመራርና ትእዛዝ ባንቀበልም፤ ቅዱስ ጳውሎስ "ህግሰ ቅድስት ይእቲ ወትእዛዛኒ ጽድቅ፤ ወሠናይ ወበረከት ውእቱ"(ሮሜ 7፡12) እንዳለው አባቶቻችችን የሰሩልን ቃለ ዓዋዲ እጅግ የምናከብረው ነው።

አባቶቻችን የሰሩልን ይህ ቃለ ዓዋዲ አሁን ከገባንበትን ችግር በራሳችን መውጣት ካቃተን የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጠው መንበረ ፓትርያርክ ነው ይላል። አባቶቻችን ክህነት ሰጭዎች ጳጳሳት ከኃብቻ ውጭ እንዲሆኑ ቢወስኑም፤ የአስተዳደር አመራሯ ግን መንግስተ ሰማያትን በሚወርሱ በተቀደሰ ትዳር የተወሰኑ ምእመናን ካህናትና መነኮሳት እንጅ፤ ከከተማ ርቀው ያሉ ገዳማት ካልሆኑ በቀር፤ ከገዳም ርቀው ባሉ በመነኮሳት፤ ያውም ደግሞ ቆሞሳት በሚባሉ ቤተ ክርስቲያናችን እንድትመራ አልሰሩም አላስተማሩንም።

አሁን ባለንበት ዘመን፤ ቀድሞ ከነበርንበት እጅግ በራቀና በከረረ ቁምስና መንፈስ፤ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ያላደጉትን ግለ ሰቦችን እየመለመሉ ፤ በሌላ ልምድ በመተዳደር ተሰማርተው የነበሩ ዓለማውያንን እያጳጳሱ ቤተ ክርስቲያናችንን የማያውቋትና ለፖለቲካ አገልግሎት ብቻ እንዲሰለፉ ተደረገ።

ቤተ ክርስቲያናችንን የማያውቁ በመሆናቸው ይህን የመሰለውን ችግር ሊፈቱ ይቅርና፤ ራሳቸው ችግር ፈጣሪዎች በመሆን የተቀደሰውን ሀላፊነት ተሸክመው በማየታችን የምናፍርባቸው ናቸው። በዚህ ምክንያት ከአገራችን ተሰደን በየደረስንበት ቤተ ክርስቲያን ስንመሰረት፤ የምንኖርበት አገር ህግ በሰጠን ነጻነት የራሳችን መተዳደሪያ ቀርጸን መተዳደር ጀምረን እዚህ ደርሰናል። ዛሬ ከቀድሞው የተሻለ ምን ተገኝቶ ነው የሸሸነውን አመራር እንቀላቀል በሚል ሰበብ ከላይ የተገለጹት መመሪያወችን የሚጣሱት ?

# <u>ከላይ የዘረዘርኳቸው መመሪያዎቻችን እንዴትና በነማን ተጣሱ?</u>

ለቤተ ክርስቲያናችን ተቀ ርቋሪ መስሎ ማሳደም ወረቀት ማሰራጨት፤ በየቦተው በመሰብሰብና በተለያዩ ሚዲያዎች ሀሰት እያሰራጩ ህዝቡን ማሸበር፤ አውደ ምህረቱን የህውከት መድረክ ማድረግ፤ ከበሮውንና ዝማሬውን ለሀሰት ማጀቢያ እውነትን ማፈኛ አድርጎ መጠቀምና ከዚያ በኋላ ቦርዱ ይውረድ የሚል ማወጅ እና በመሳሰሉ ስርአተ አልበኞች ተጣሱ። ጌታችን "የተደበቀ ምሥጢርም ሳይከሰት አይቀርም "(ማቴ 10፡26) እንዳለው፤ እስካሁን አፍኜ ማያዜ በፍርሀትም ሆነ በትእግስት ቢተረጎምብኝም ይቅርታ እየጠየኩ፤ አሉባልተኞች በሚያሰራጩት የስም ማጥፋት ዘመቻ፤ ሰውን ለመታደግና፤ እራሳቸውንም በራሳቸው ስለገለጹ፤ ባለብኝ ሀለፊነት ስም በመጥራት ያየሁትን የታዘብኩትን ስህተቶችንና የፈጻሚዎችን ድርጊቶች ለመግለጽ ተገድጃለሁ። "ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ ይፈለግበታል። ብዙ አደራ ከተሰጠውም አብዝተው ይሹበታል"( ሉቃስ 12፡48) እንዳለው ብዙ ሀላፊነትና ብዙ የሚጠበቅባቸውን ክቡር ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህንና ዶ ክተር አከሊሉን እጠቅሳለሁ።

# <u>ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ</u>

ዓውደ ምህረቱን ለማስከበር የገባነውን ቃል ጥሰው ከተሳሳቱት ሰዎች ጎን በመቆም አውደ ምህረቱን የጫጫታ ማስፈጸሚያ ማድረጋቸው፤ በሽምግልናቸው የሀሰት መጋረጃ በመሆን አይሳሳቱም ብሎ የሚያምንባቸውንም ህዝብ በማሳሳታቸው፤ በምወዳቸውና በማከብራቸው አባቴ በሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ ላይ ከሁሉም ይልቅ እጅግ በጣም እጅግ አዝኛለሁ።

እርግጥ ነው በአዲስ አበባ ከተማ ብንገናኝም በእድሜ እንደምንራራቅ የመጣነው ጉዞም አንድ አይነት እንዳልሆነ እገነዘባለሁ። ለተወሰነ ጊዜ አዲስ አበባ አብረን ብንቆይም፤ ይህን የመሰለ ፈታኝ ነገር ገጥሞን አብረን በመሰለፍ ፈተናውን አሸንፈን የወጣንበት ጊዜ እንዳልነበረ አውቃለሁ። በእርግጥ አውቃቸው ነበር ለማለት እንዳልደፍር ሆኛለሁ።

ይሁን እንጅ በእድሜ ያላቸውን ጸጋ ሳልነካ እያከበርኩና ከቤተ ክርስቲያን በላይ ግን ማንም መከበር እንደሌለበት እየገለጽኩ፤ ያየሁትን ስህተት ስመሰክር ክብር መንካት አባትነታቸውን ዝቅ ማድረግ አለመሆኑን ተመልካችና ሰሚ እንዲገነዘብልኝ በትህትን እጠየቃለሁ። ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸውን ምእመናን በተንኮልና በአድማ በጠሉት ሰው ላይ እየቀሰቀሱ ለማስጠላት የሚጠቀሙበትን ተንኮል፤ የምእመናን ጥላቻ በኔ ላይ ለመከስከስ ካነሱት ጋራ መተባበራቸው እኔን ሳይሆን ህዝቡንም ቤተ ክርስቲያንን ጎዷት።

ሰሞኑን የተቀሰቀሰው ጉዳይ፤ ከ10 አመታት በፊት በከንሳስ ተከስቶ ወደኛ የደረሰው በወቅቱ መላ ኦርቶዶክሱን ያነጋገረው ነገር ነው። ባካባቢያችን እንደ አዲስ ተነስቶ በተሳሳተ መንገድ በመሰራጨት ለሀሰት ክሳቸው ማዳበሪያ አድርገው ማቅረባቸውን በሩቅና በቅርብ ሆኖ ለሚመለከተው ሁሉ መገለጽ እንዳለበት ወቅቱ ያስገድዳል።

ከ 10 አመታት በፊት ከንሳስ በሚኖሩት ምእመናን መካከል በዚህ ጉዳይ ውዝግብ ተነስቶ የተሳሳቱ ሰዎች ትልቅ ውዝግብ ተፈጥሮ ነበር። እነዚህ የከሰሱ ሰዎች ይህን ጉዳይ ለክሳቸው ማደበሪያ በማድረግ ያልተረዳውን ህዝብ በመቀስቀስ ጫጫታውን ቀጠሉ። የጉባዔው አባላት በግል ጥቅም በሹመት እየተደለሉ ቢያፈርሱትም በዚያን ጊዜ የካህናት ጉባዔ ነበር። <u>ጉባዔውን በሊቀ መንበርነት የሚመሩት ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ነበሩ</u>።

የከንሳስን ኪዳነ ምህረት የመሰረቱት አቡነ ይስሀቅ ነበሩ። እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ህግና ስርአት በአዋቂዎች ሳይመረመር በወጣቶች ጫጫታ እየተመሩ አቡነ ማትያስ አግኛለሁ ማለታቸው ከቀኖናችን ውጭ በመሆኑ በካህናቱ ጉባዔ እንዲታይ አቡነ ይስሀቅ ለሊቀ መንበሩ ለሊቀ ሊቃውንት ሀሳብ አቀረቡላቸው። ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህም በሊቀ መንበርነት የሚመሩት ጉባዔ ስህተቱ የአቡነ ማትያስ እንደሆነ ተረዳ። ከንሳስ ላይ ሚንጫጬት ወጣቶች የሚከተሉት ትምህርትና እምነት በሊቃውንቱ የማይታምንበት፤ የቤተ ክርስቲያናችን አቻዎች የግብጽ የህንድ የአርመንና የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት የማይቀበሉት መሆኑን ተረዳን።

ጉዳዩ እልባት እንዲሰጥበት "እስከ ዛሬ ወልድ ዋሕድ በማለት አንድ ሆነን ከኖርነው ከአራቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ያለንን የነገረ ሃይማኖት አንድነት እንዳያስቀርብን ብሎም እንዳይለያየን. . . እናት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ ስትጠቀምበት የነበሩትን ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቀድሞ ሊቃውንትን እምነት ባገናዘበ ሁኔታ የማያዳግም ውሳኔ ይስጥበት" የሚለውን በሊቀመንበርናታቸው አስወስነው ለአቡነ ጳውሎስ፤ ለሲኖዶስ፤ ለራሳቸው ለአቡነ ማትያስና ለአቡነ ይስሀቅ ያቀረቡት እራሳቸው ሊቀ ሊቃውንት ነበሩ። (*ሙሉ ማስረጃውን ከፈለጉ ይህን በመጫን ይመልከቱ። (ሙሉ ማስረጃውን ከፈለጉ ይህን ይጫኑ*።)

የከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን መሥራች አባት የነበሩት አቡነ ይስሐቅም፥ የውሳኔውን ትክክለኛ ግልባጭ በቤተ ክርስቲያናችን እምነትና በቅዱሳት መጻሕፍት በተደገፈው በተዋሕዶው እምነታችሁ በመቆም ከዚህ ቀደም በነበራችሁ ፍቅርና አንድነት ጸንተው የተቋረጠውን አገልግሎት እንዲቀጥሉ ለከንሳስ ህዝብ በደብዳቤ አረጋገጡ ።( *ሙሉውን ማስረጃ ከፈለጉ ይህን ይጫኑ*)

ጉዳዩ ተብራርቶ ለህዝብ ቢቀርብ በመንግስት ድጋፍ የተሰየሙትን የሚያስወቅስና ከመንበራቸውም የሚያወርዳቸው ስህተት መሆኑን ስለተገነዘቡ "ውሾ ን ያነሳ ውሾ ይሁን" በሚል መርህ ቢያፍኑትም አንዳንድ ግብረ ገብነት የገደላቸው አሉባልተኞች፤ ያለውን መከፋፈል በመጠቀም የቅድስት ድንግልን ስም እጅግ በተሳሳተ መንገድ እያነሱ የህዝብ መከፋፍያና የጠሉትን ሰው የመጉጃ መሳሪያ በማድረጋቸው፤ ይህ እንዲቆም የከንሳስ ህዝብ ወደ አኃት እና ምስራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት አቀረቡት።

ይህ የተነሳ ትምህርትና እምነት የራሳችን ሊቃውንት አበው የሚያስተምሩትና የሚያምኑበት ብቻ ሳይሆን ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ጋራ አቻ የሆኑትን አራቱ እህት አብያተ ክርስቲያናት የሚያምኑበት፤ የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚስማሙበት መሆኑን ሁሉ

መስከሩ። ይልቁንም የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይህን የሚያስረዳ ልኡክ ወደ ከንሳስ በመላክ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ በፊርማቸው ለሚመለከተው ያቀረቡት ትምህርትና እምነት ትክክለኛ የኦርቶዶክስ ትምህርትና እምነት እንደሆነ አረጋግጠዋል።

አንዳንድ እምነተ ጎደሎዎችና ሞራለ ቢሶች ባጋጣሚ ጉዳይ ከጓደኞቻቸው ጋራ ሲጋጩ፤ በውሳኔ የታለፉትን ጉዳዮች እያነሱ ማጥቂያ አድርጎ ማቅረብ የተለመደ ርኩስ መንፈስ ነው። አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ይህን ርኩስ መንፈስ የወረሱ የሰንበት ተማሪዎች፤ ከአባ ሰረቀ ጋራ ባስተዳደር ሲጋጩ በሊቀ ሊቃውንት ሰብሳቢነት በተደረገው ጉባዔ ላይ ስለነበሩ ማህበረ ቅዱሳን ላቀረበባቸው ክስ ማዳበሪያ አድርጎ አቀረቡባቸው። አባ ሰረቀም በወቅቱ የተካሄደውን ሁሉ የጽሁፍ ዘገባ ሰብስበው "እውነትና ንጋት" በሚል አሳትመው በቤተ ክህነቱ አስመረቁት። የሚከተሉት እምነትም ትክክል እንደሆነ እንዲረጋገጥ አስደረጉ። (ለማንበብ የሚከተለውን ሰንሰለት በመጫን ያንብቡ። በአባ ሰረቀ ላይ ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ።

(ደብዳቤውን ለማንበብ የሚከተለውን ሰንሰለት በመጫን ያንብቡ። አባ ሰረቀ የተከሰሱበትን ነፃ የሚያደርግ ከቅዱስ ሲኖዶስ የተጻፈ ደብዳቤ)

የሚያስገርመው ነገር በቤተ ክርስቲያናችን ጣልቃ የገባው መንግስት ደግሞ ይህ ዘገባ የቀረበባቸው አቡነ ማትያስን ፓትርያርክ አድርጎ ሰየማቸው። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ከላይ እስከታች የሚደገረገውን ሰይጣናዊ እንቅስቃሴ ነው።

አሁን በዚህ ሰሞን በአቶ አዲሱና በሊቀ ሊቃውንት መሪነት በተፈጠረው ውካታ ተነትተው የገቡ ወጣቶች በህዝብ የተመረጠውን ቦርድ አፍርሰው እነሱ እንዲቆጣጠሩት በፈጠሩት እንቅስቃሴ ባለመተባበሬ፤ ራሳቸው ሊቀ ሊቃውንት ከ10 አመታት በፊት በፊርማቸው አረጋግጠው ለሚመለከተው ሁሉ ያቀረቡትን ነገር አንስተው በኔ ላይ ላቀረቡት ክስ ማደበሪያ ማድረጋቸው ይቅርታ የሌለ በደል ነው። ህዝቡ አይደርስበትም በማለት ደካማ አስተሳሰብና በህዝብ ማስተዋል ላይ ባላቸው ንቀት፤ ሊቀ ሊቃውንት ራሳቸው በመሩት ጉባዔ፤ ራሳቸው አስወስነው በራሳቸው ፊርማ አረጋግጠው ለሚመለከተው ሁሉ ያቀረቡትን በኔ ላይ ሊጭኑት መመኮራቸው ሽምግልናቸውን የሚንድ ከክህነታቸውን ከጥያቄ ላይ የሚጥል ነው።

ከላይ እንደገለጽኩት በብዙ ማስረጃ ትክክል ሆነ የተገኘውን ቀርቶ፤ ስህተት እንኳ ሆኖ ቢገኝ፤ ከሁላችንም ይልቅ መወቀስና መከሰስ ያላባቸው በሰብሳቢነት ጉባዔውን የመሩትና በፊርማቸው ለሚመለከተው ሁሉ ያቀረቡት ራሳቸው ሊቀ ሊቃውንት ናቸው። አሁን በራሳቸው በሊቀ ሊቃውንት የሚመራው ቡድን የሚፈጽመው ሁሉ ክስና ወቀሳ የተሳሳተ መሆኑን ለማሳየት ይህ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል። ወደ ዶክተር አክሊሉ እሻገራለሁ

## ዶክተር አክሊሉ

ዶ ክተር አክሊሉ በእድሜያቸው ሊወልዱኝ ይችላሉ ለማለት ባላረጋግጥም፤ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩንቨርስቲ ፕሬዝደንት በነበሩ ጊዜ የነበርኩበትን ሳስብ ሊወልዱኝ እንደሚችሉ እገምታለሁ። ዛሬ የራሴ ጓደኞች በብስጭትና በበሽታ እያለቁ በህይወት ያሉት ጥቂት ናቸው። ከሳቸው እጅግ ትንሽ በሆነው እድሜየ በየደረስኩበት የሰራሁት በደልና ስህተት እየከበደኝ ነው። የምገባበት መቃብርም እየቀረበብኝ ነው። በቀረችው ዘመን ሳልዋሽ ህሊናየን ሳላታልል እንድፈጽማት ከራሴ ጋራ በመታገል ላይ ነኝ። ከእሳቸው ይህን በማጣቴ እጅግ አዝኛለሁ።

መሳሳታቸውን እንዲያቀሙ በግል መክሬያለሁ። በቤተ ሰብ ፊትም እንዲያቀሙ ተናግሬያለሁ። ነገር ግን ራሳቸውን ከክርስትናውና ከመመሪያችን በላይ አድርገው በመገመታቸው ከዚህ ስህተት ላይ ሊወድቁ ችለዋል።

"እለ የሃድጉ ሕገ ይዌድስዋ ለኃጢአት" (ተግሳጽ 28፡4) ማለትም ህግንና ስርአትን የሚሽሹ ሰዎች ኃጥአንን ይደግፋሉ እንዳለው ተግሳጽ፤ በግል ስሜታቸው እየተገፉ በሚፈጽሙት ተደጋጋሚ ስህተት ራሳቸው ካዘጋጁት ደንብና መተዳደሪያችን ጋራ ተጋጩ። እንዲንጫጩ ያነሳሷቸውን የሰዎችን ጫጫት በመጠቀም በህግና በስርአት የተመረጠውን ባለ አደራ ቦርድ ይውረድ ብለው በዓውደ ምህረቱ ላይ አወጁ። "ወአናቅጽ ሲኦል ኢይሄይልዋ" የተባለችውን ቤተ ክርስቲያናችንን ከአህያ ቆዳ የተሰራች በጅብ ጩኸት የምትፈርስ ቤት ሊያደርጌት ሞከሩ።

እንደሳቸው ያለ አዛውንት ለራሳቸው ክብርና ዝና በመፈለግ፤ እኔ በማዝዘውና በፈለጉት መንገድ ካልተሄደ አፈርሳለሁ እበትናለሁ ብሎ ታጥቆ መነሳት ለሳቸው ብቻ አይደለም ለሁላችንም ሀፍረት ነው። "ከመ አፍ እንተ ትሠርር እማህደራ ከማሁ ብእሲ ይትቀነይ ሶበ ይነግድ እምብሔሩ"(ተግ 3፡8) ካገሩ ከመንደሩ ከደብሩ የተፈናቀለና መፈናቀሉን ተቀብሎ የሚበትን ሰው በወንጭፍ የሚባረር የማሽላ ወፍ ነው። የሚለውን ማስተማርና እንዳይበተን መጣር የሚገባቸው ሲሆኑ ከነ አቶ አዲሱ ጋራ በመተባበር ተቃራኒውን አደረጉት። "ይጎይይ ረሲእ

እንዘ አልቦ ዘይዴግኖ” (ተግ 4፡1) እንዳለው ፤ አቶ አዲሱና መሰሎቹ ቀደም ብለው ሲያጠራቅሙት በኖሩት በደልና ኃጢአት ከቤተ ክርስቲያናችን ተሰናብተዋል።

ሁሉንም አስክሮ ከዚህ ያደረሳቸውን ተነግሮ የማያልቀውን ስህተታቸውን እያከታተልን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ደህንነትና፤ በሚረጩት ሀሰት ህዝብ እንዳይበከል ስንል ወደፊት በማከታተል እንገልጻለን።

እነዚህ ሁሉ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የግል ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ የኢያሪኮ ቅጽር የፈረሰችበትን የጫጫታ ዘዴ በመጠቀም ቤተ ክርስቲያናችን ለማፍረስ ታጥቀው የተሰለፉ ናቸው። የኢያሪኮ ቅጽር የፈረሰበት ጫጫታና ተመልሶ የተገነባበት፤ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችንን ለማፍረስ የሚደረገውን ጫጫታ ሙሉ በሙሉ ስለማይገልጸው፤ በተቃራኒ እንጅ በተመሳሳይ አንጠቅሰውም። በኢያሪኮ አፈጻጸም ላይ የተደረገው ስህተት ያስከተለው መቅሰፍት በእኛ ላይ እንዳይደገም እንድንጠነቀቅ ማሰሰብ እወዳለሁ ። (1 ኛ ነገ 16፡ 34 )

## ልንጠነቀቅ የሚገባን

በጫጫታ የተናወጠውን የኢያሪኮ ቅጽር በቅድሚያ ሊደረግ የሚገባው ነገር ሳይከናወን መልሶ ለመገንባት በሞከረ ሰው ላይ የደረሰው ቁጣና መቅሰፍት እንዳይደርስብን በረጋ መንፈስና በማስተዋል ልንጠነቀቅ ይገባል።

“ከመ ንፈጽም ዛተ ኩሎ ዕለተ፤ ወኩሎ ቅንአተ፡ ወኩሎ መከራ፡ ወኩሎ ግብረ ሰይጣናት፡ ወምክረ ረሲአን እኩያን ወእምትናሳኤ ጸር ዘህቡእ ወዘገሀድ አርህቅ እግዚአ እምኔየ፡ ወእምነ ኩሉ ህዝብከ፤ ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ “ (ሥ ቅ ገጽ 32፡ ቁ33__38) እያልን እንጸልያለን። ይህም ማለት “አምላካችን በየእለቱ ልንፈጽማቸው የሚጋባንን በጎ ተግባር ለመፈጸም እንቅፋት የሆነን በምቀኝነት በተለያዩ የፈተና አይነቶች በስውርና በገሀድ የሚደርሱብንን ሁሉ የሰይጣናት ስራና አድማ የጠላትን እንቅስቃሴና ሰልፍ ከኛ አርቅ፤ ከህዝብህ ሁሉ አርቅ ከዚህ ቅዱስ ቦታ አርቅልን እያልን የምንጸልየውን አምላካችን ተቀብሎ ከእያንዳንዳችን ህሊና ጀምሮ የጎደፈውን ቤተ መቅደስና ዓውደ ምህረቱን ለማጽዳት እንደሆነስ ምን እናውቃለን?

ለማፍረስም ሆነ ለመገንባት የምንወስዳቸው ርምጃዎች በጫጫታ ከሆነ ከአምላካችንና ከመመሪያችን ጋራ እንጋጫለን። ለሀጣን የወረደ ለጻድቃን የሚተርፍ መቅሰፍት ይሆንና፤ መጨረሻው ጸጸትና ሀዘን ነው። ስለዚህ የገጠመንን ነገር ረጋ ብለን በቅዱሳት መጻህፍት በቀኖና በቃለ አዋዲው እና በመተዳደሪያ ደንባችን መሰረት በጥንቃቄ ልንመለከተው ይገባናል።

የሚነሱትን ነገሮች በጥንቃቄ በመመርያ ደንባችንና እግዚአብሔር በሚፈቅደው መንገድ መወሰን ሲገባን አለባብሰን እውነትን ደብቀን ወደ ጥገናውና ወደ ግንባታው ብንሄድ በጫጫታ የፈረሰችውን ኢያሪኮን መልሶ ለመገንባት በሞከረው ሰው ላይ የደረሰው መቅሰፍትና ሀዘን ይደርስብናል።

በጫጫታ የፈረሰችውን ኢያሪኮን ነገሮ ችን ሳይመረምር ሊደረግ የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት ሳያደርግ ለመገንባት በሚሞክር ሰው ላይ ”ኢያሱ ይህችን ከተማ መልሶ የሚገነባ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተረገመ ይሁን“ (6፡26) ብሎ ውግዘትና መርገም አስተላለፈ።

ኢያሱ እንዳለው፤ አኪኤል የተባለ ሰው በቅድሚያ ሊከናወን የሚገባውን ሳያስቀድም ኢያሪኮን ሊሰራ መሰረቱን ሲጥል የበኩር ልጁ ሞተ። የቅጽር በሮቿን በሚሰራ ጊዜ ደግሞ የመጨረሻ ልጁ ሞተ። ይህንንም በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት ምዕራፍ 16፡ ቁጥር 34 ላይ ተመዝግቦ እናነበዋለን። መቅሰፍቱን ያስከተለው የፈረሰው በመሰራቱ ሳይሆን፤ መደረግ ያለባቸው ቅድመ ዝግጅቶች ባለመደረጋቸው ነበር።

ከተንኮል ከሀኬት ከአድማ አንድነታችንን ሳናጸዳ ወደተቀደሰ ነገር መቅረብ በየተቀደሰው ነገር ተቀላቅሎ የሚውጠውን የሚፈልገው እንደ አንበሳ የሚያገሳው ዲያብሎስ ወደ ይሁዳነት ይለውጠናል። በጸሎተ ሀሙሱ ስርአት ላይ በተንኮል የሸመቀ ህሊና ይዞ በተሳተፈው በይሁዳ፤ ሰይጣን መንፈሱን ከህብስቱ ጋራ ቀላቅሎ የከተተበትን ማጤን ያስፈልገናል።

መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅታችሁ አስፈላጊውን አሥራት ሳታቋርጡ እየከፈላችሁ ይህንን ቦርድ መርጣችሁ የሰየማችሁ ምእመናን፤ ካቅም ማነስ ምክንያት ደንባችን የሚጠይቀውን ባለሚሟላታችሁ፤ ባለ አደራውን ቦርድ ለመሰይምም ሆነ ለመሻር መመሪያችን ባይፈቅድላችሁም፤ ችግር ናቸው የተባሉትን ነገሮች ባለ አደራ ቦርዱና ደንቡ የሚፈቅድላቸው አባላት በእውነትና በቅን መንፈስ የሚያስተላልፉትን ውሳኔ በጸሎት በሀሳብና በምክር የመደገፍ እድሉ አላችሁ።

ውሸቱን ውሸት፤ እውነቱን እውነት፤ ሳንልና አድበስብሰን በማለፍ ሰላምን እናምጣ ብሎ የሚሞክር ካለ ቤተ ክርስቲያንን የበለጠ መበደል ነው። የአምልኳችንና የጸሎታችን መነሻና መድረሻ "ሰላም ለኩልክሙ" የምንልባት በእግዚአብሄር ቤት ይቅርና በዓለማዊ ጉዳዩችም ቢሆን ነገሮች የሚስማሙት እውነትና ሰላም በተወሀዱበት ነው። ሀሰትንና ሰላምን ቀላቅሎ ወደ መፍትሔ ለመድረስ መሞከር፤ የማይስማሙትን ጠምዝዞ ወቅቱን ጠብቆ የሚፈንዳ ቦምብ በህዝብ መካከል መቅበር ነው። "እግዚአብሄርን በቁጣ የሚያነሳሳ ነው። በነሙሴ ዘመን የነበረ እግዚአብሔር የዛሬው ነው። የነገውም ነው። ስለዚህ በዚያ ዘመን የተፈጸመው መቅሰፍት ዛሬ አይፈጽምም ብየ አላምንም። የተሰራጩ ሀሰት ሳይጣራ ዝም ብሎ አድበስብሶና አለባብሶ ማለፍ የሚያስከትለው መቅሰፍት ያስፈራኛል። በዚህ ጉዳይ ለተነካካው በተለይም ሳይገባቸው በሰዎች ግፊት ዘለው በመግባት ጫታታውንና ውካታውን ለሚያስተጋቡት ወጣቶች ስርአት ገደብ ይኑራችሁ እያልኩ፤ ከዚህ መቅሰፍት ላለመሳተፍ አድበስብሶ ና አስመስሎ ከማለፍ እራሴን እንዳገል እገደዳለሁ።

## <u>ባልገባችሁ ነገር ተጠልፋችሁ ለጥፋት መሳሪያ በመሆን ጫታታውንና ውካታውን በማስተጋባት ላይ ያላችሁ ወጣቶች ሆይ</u> !

ባልገባችሁ ነገር በተንኮለኞች እየተገፋችሁ በስርአት የተመረጠውን ቦርዱን ለማፍረስ በሚራወጡት ተንኮለኞች እየተገፋችሁ መዝሙራችሁንና ከበሮውን የእውነትን እስትንፋስ ለማፈን የሞከራችሁ የሰንበት ተማሪዎች ተጠንቀቁ! መጀመሪያ ፈሪሃ እግዚአብሔ ይኑራችሁ። የቤተ ክርስቲያናችሁን ቀኖና እና መተዳደሪያ ደንባችን ተረዱ። ለቀኖናው፤ ለአውደ ምህረቱ፤ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ባለንብረት ለሆነው ለጠቅላላው አባልና ለመረጠው ባለ አደራ ቦርድ ተገቢውን ክብር ስጡ። ለማፍረስ እንቅስቃሴ በጀመሩትና በሰሩት ስራ፤ የክህደት መጽሀፍ ሸጦ ለመክበር ባሳዩት ስግብግብ ባህርይ ከቤተ ክርስቲያን በተሰናበቱት ሰዎች እየተገፋችሁ ህዝብ የምታደነቁሩበትን ጫጫታ አቁሙ።

"አ ወ ልድየ ኢያስህቱከ ሰብእ ረሲአን። ወኢትፍቅድ አመ አስተበቁዑከ እንዘ ይብሉ ነዓ ምስሌነ ተሳተፍ ደመነ። ወንድፍ ውስተ ምድር ብእሴ ጻድቀ በንምላእ አብያቲነ በበርብሮ ወአንተኒ ህበረ ምስሌነ ። ኢትሁር ምስሌሆሙ ፍኖተ ።እስመ ለእከይ ይረውጽ እገሪሆሙ 10-16) ብሎ ሰሎሞን በሰጠው ምክርና ተግሳጽ ባትቀበሉትም ያባትነቴን ድርሻየን ለመወጣት እመክራችኋለሁ። ይህም ማለት፤ ልጆቼ ሆይ መንፈሰ ጎስቋሎች አያሳስቷችሁ፤ ባድማችን ተባበሩንና እውንትን እናጥፋት በሚሏችሁ ሰዎች በመታለል በአድማቸው ከተው ሊፈጽሙ የፈለጉትን ጥፋት ለመፈጸም መሳሪያ እንዳያደርጌችሁ ተጠንቀቁ! ምክሬን ብትሰሙ የምትጠቅሙት እራስችሁን ነው፤ ምክሬን ባለመስማት የጥፋታቸው መሳሪያ ብትሆኑ፤ አምላክ ከማይወደው ሀሰት ጋራ በመሰለፋችሁ በሥጋና በነፍስ ትጎዳላችሁ።

ይህች ወቅት አልፋ በተረጋጋ መንፈስ አሁን የምታስተጋቡት ረብሻና ጫጫታ በህግና በስርአት መገታቱ ስለማይቀር፤ በዓውደ ምህረቱ ላይ የፈጸማችሁትን ጫጫታና ረብሻ መለስ ብላችሁ በረጋ መንፈስ ስታቃኙት እድሜ ልካችሁን የሚያጸጽታችሁ መሆኑን በቅድሚያ አሳስባችኋለሁ።

ምኞታቸውን እንድትፈጽሙ የቀሰቀሷችሁ ሰዎች ሊያገኙት በማይችሉት በሙዳየ ምጿቱ ላይ ዓይናቸውን የተከሉ፤ በህዝብ ተመራጭ ቁጥጥር አንመራም ያሉ፤ በሙዳየ ምጿቱ የጎመጁና የሰከሩ በመጨረሻም ያላንዳች ህዝባዊ ታዛቢ ገንዘቡን ለመዝረፍ የፈለጉ፤ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በስርአትና በህግ የሚጠብቀውን ቦርዱን ለማስወገድ ታጥቀው የተነሱ ናቸው።

እነዚህ "እመ አውተርከ ዓይነ ህሊናከ ለዕለ ንዋይ ወብእል ኢትክል ረኪቦቶ፤ ባሕቱ ይከውን ከመ ንስር ዘይሰርር ኀበ ደመና ሰማይ"( ምሳሌ 23፡ 4-5) የሚለውን ተግሳጽና ምክር የማይቀበሉ ናቸው። ይህም ማለት፤ "ማግኘት በማይገባህ ገንዘብ ላይ ዓይነ ህሊናህን ብታፈጥ፤ አታገኘውም" የናንተን ጫጫታ ተጠቅመው፤ የንብረቱ ባለቤት ምእመናኑ ንብረታቸውን እንዲጠብቁላቸው የሰየሟቸውን ባለ አደራ ቦርድ ይወገድ የሚለውን በማሰማት ላይ ያሉ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ለህዝቡ አስበው ሳይሆን ዘርፈው ለመክበር ታጥቀው የተነሱ ናቸው።

## <u>ሰሞኑን በአውደ ምሕረቱ ላይ ባያችሁት በሰማችሁት ያዘናችሁ አባቶች እናቶች ሆይ!</u>

ችግሩን የፈጠሩ ሰዎች ሳይመቻቸው በድብቅ፤ ሲመቻቸው ደግሞ በገሀድ የሐሰትና የጥላቻ አሉባልታ በወረቀትና በቃል ማሰራጨት ከጀመሩባት ቅጽበት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሲያካሄዱት የነበረውን ለመግታት በግልም በጋራም ስትመከሩ፤ ስትገስጹ በመታገል ያባትነትና የናትነት ሀላፊነት ተወጣኋልና አይጸጽታችሁ። የናንተን ምክርና ተግሳጽ ከመስማት ይልቅ በክፋታቸውና በኃጢአታቸው በሰከሩ ሰዎች አድማ ተጠልፈው በዓውደ ምህረት በመንጫጫት ላይ ያሉትን ወጣቶች ወላጆቻቸው ቢያዩዋቸው ከምን አይነት ዘመን አደረስከን? እነዚህን ጉዶች ከመውለድ ማህጸናችን በደረቀ ብለው ከእናንተ ጋራ እንደሚያለቅሱ የታወቀ ነገር ነው።

ወጣቶች በተለይም ሴቶች ወጣች፤ ያለ ምንም ይሉኝታና ሀፍረት መረን በለቀቀ ባህርይ በአውደ ምህረቱ ላይ ባሳዩት ጩኸትና እንቅስቃሴ ያዘናችሁና ያለቀሳችሁ አረጋውያን አባቶች፤ እቤራት እናቶች መንፈሳችሁ በመንዳቱ እጅግ አዝኛለሁ። አሁንም ባይሰሟችሁም፤ ቢዘልፏችሁም ምክራችሁን ከመስጠት አትሰልቹ። እግዚአብሄር እንዲመልሳቸውም ጸሎታችሁን አታቋርጡ።

ጠቅላላ ምእመናን ሆይ እኔ በበኩሌ "አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! እግዚአብሄር ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ ! ዛሬ የምታዩቸውን ግብጻውያን ዳግም አታዩዋቸውም" እያለ ሙሴ የተናገረውንና የተመራበትን ለመተግበር እየታገልኩ ለሚሰሙኝ ሁሉ ከማካፈል ያየሁትን ከመመስከር ያለፈ ኃይል የለኝም። ኃይል የእግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጸው በእምነትና በሞራል ጸንቶ በሚቆም ህዝብ ነው።

"ዛሬ የምታዩቸውን ግብጻውያን ዳግም አታዩዋቸውም" የሚለውን በመከተል፤ መከራውንና ፈተናውን ስላከበዱብን መታገስ ሰልችቶን ፊታችሁን እስከ መጨረሻ አታሳየን ከሚል ደረጃ ላይ መድረስ ባይገባንም። ሙሴ "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል። እናንተ ያለባችሁ መታገስ ብቻ ነው" (ዘጸ 14፡14) እንዳለው፤ በፈሮን ሠራዊት ላይ የደረሰው መስጠም ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠም በሚንጫጩት ሰዎች ላይ እንዲደርስባቸው ሳንመኝ፤ ነገር ግን ከገቡበት አድማና ስምጠት ወጥተው እንድናያቸውና ተጸጽተው አብረውን እንዲቆሙ እንመኝላቸዋለን። "እናንተ ያለባችሁ መታገስ ብቻ ነው" "አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! እንዳለ በእግዚአብሄር በራሳችን ህሊናና በቅዱሳት መጻህፍት በቃለ ዓዋዲውና በመመሪያችን ጸንተን በመቆም በእግዚአብሔር ላይ የከፈቱትን ውጊያ እግዚአብሔር የሚመልሰውን አጻፋ መመልከት ነው።

እግዚአብሔር ካሸባሪዎች ጋራ እንዳልሆነ ከሚሸበሩት ጋራም አይደለም። እግዚአብሄር የሚኖረውና የሚሰራው አይዞህ ጽና እጅግም በርታ የሚል መንፈስ ካለው ህዝብ ጋራ ብቻ ነው። (ኢያሱ ፤፡ 2__9) በህግና በሥርአት እንዲከናወኑ የሚፈለጉ ሁሉ ነገሮች የሚፈጸሙት፤ ከተቆመበት እምነት ጽናትና መመሪያ እየተሸበሩ በመናወጥ፤ ወደ ግራና ወደቀኝ በሚወላውል ህዝብ አይደለም። ስለዚህ በእግዚአብሄር መታመን፤ የራስ ህሊና ማጽናትና ከመመሪያዎቻችን ዝንፍ ላለማለት መጠንቀቅ ነው።

"ከመ መንኮራኩረ ሰረገላ ልቡ ለአብድ ወከመ መንኮኮት እንተ ተአውድ ከማሁ ምክሩ ለፈራህ"(ሲራክ 36፡5) እንዳለው ሲራክ፤ መሸበር አምላክን መርሳት፤ ራስን፤ መመሪያንና እውነትን መጠራጠር ነው። የሚጠራጠር ሰው "በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባህር ማእበል ይመስላል። በሁለት ሀሳብ የሚወላውል ከእግዚአብሔር ምንም ነገር እንደማያገኝ ሐዋርያው የዕቆብ ተናግሯል። (፤፡6__8)

ሱኑትዩ የተባለው ሊቅም "ወንሕነሰ ንትወከፍ ትምህርታቲሆሙ ዘመህሩነ ወነአምን ቃላቲሆሙ ዘተፈነዎ ለነ እምኔሆሙ ወእሁዛን በትምህርትነ ዘተምህርነ ወጽኑአን ንህነ እንበለ ተወላውሎ.. . . " (110; 14) ይህም ማለት; ከቅዱሳት መጻህፍት ከሊቃውንት ምክርና ከመመሪያችን በመወላወል አንዋዥቅ እያለ ተናግሯል። ወገኖቼ በዚህ ዘመን ከሀገራችን ሸሽተን ብንሰደድም፤ በአገራችን ላይ የሚነደው የመከራ እሳት እየተከተለን ነው። በኛ ላይ የደረሰው ፈተና በአገራችንና በጎረቤት አገር ተሰዶ በሚኖረው ህዝባችን ላይ ከሚደርሰው መከራ ጋራ ሲነጻጸር እጅግ ቀላል ቢሆንም፤ ከመጀመሪያ ጀምሮ በቅርብ ሆኜ ስላየሁት ይመስለኛል፤ በግሌ እንደዚህ የከበደኝ፤ ያስጨነቀኝና ያሰፈራኝ ፈተና ውካታ ገጥሞኝ አያውቅም። በቅርብ በሩቅም የምታውቁኝ ወገኖቼ እንደዚህ መሮኝና ከብዶኝ የተናገርኩበት ጊዜ ያለ አይመስለኝም። ያየሁትና የታዘብኩት ሸፍጥ፤ ተንኮልና ሀሰት ሞልቶ ልቆጣጠረው ባለመቻሌ እንደሆነ መረዳት የሚሳናችሁ አይመስለኝም።

በተረፈ ወገኖቼ ሆይ! <u>"አትሸበሩ ጸንታችሁ ቁሙ! እግዚአብሄር ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ ! ዛሬ የምታዩቸውን ግብጻውያን ዳግም አታዩዋቸውም ! " (ዘጸ 14፡13) በሚለው ቃል ጸንታችሁ እንድትቆሙ አደራ በማለት ሀላፊነቴን ለመወጣት ምክሬንና ምስክርነቴን አቅርቤላችኋለሁ።</u>

"እግዚአ አዕምሮ ወዜናዌ ጥበብ" እያልን የምንማጸነው አምላካችን የተሰወረውን ይግለጽልን !